# የተናገሩት ከሚጠፉ

ህገወጥ ቤት፣ የጨረቃ ቤት፣ ቦታው ለሌላ ጉዳይ የሚፈለግ ወዘተ እያሉ የአዲስ አበባን ነዋሪ ቤታቸውን በላያቸው ላይ እያፈረሱ ቤት አልባ ማድረግና ትውልድ ማምከን በጣም የሚያም ነገር ነው። የሚሆነው ሁሉ እየሆነ ያለው፣ ያለ አፈ ቅቤ ጠቅላያችን፣ በደመቀ ጭብጨባና በመደመር ጭምብል የመጣው ብዙ ያለውና ብዙ ተስፋ የተጣለበት ዶ ር አብይ ይሁንታ ነው ብየ ለማመን እቸገራለሁ። ያ ሁሉ ከተቃዋሚ አፍ ሰብስቦ በግልፅና በማያሻማ ቋንቋ የተናገረው በጎ ቃል ሁሉ የት ገባ?



የ ነአብይ መንግስት - በጭብጨባ አደገ

ተ ስፋ የጣለን ህዝብ - ቤት አልባ አደረገ

ና ቁና አዋረዱት - ቤታቸው ፈረሰ

ገ ናናውም ቃሉ - በደም ተለወሰ

ሩ ብ ዘመን ገፍተን - አዲሱ ሲመጣ

ት ላንት የገባውን - የተስፋ ቃል አጣ

ከ ዳ ያመነውን - ህዝብ አምኖት ነበረ

ሚ ዛን አልባ ሲሆን - አገር ተማረረ

ጠ ራርጎ አባረረ - ጥላቻው ከረረ

ፋ ና ወጊ መስሎ - ህዝቡን አሸበረ

የ ኢህአዲግ ነገር - ዱሮም ልማዳቸው

ወ ረው ማፈናቀል - ሆነና ግብራቸው

ለ ፍተው የሰሩት ቤት - ፈርሶ በላያቸው

ዱ ካቸው ሲጠፋ - ዛሬም አየናቸው

ት ላንት አዲስ አባ - ወጥቶ ደግፏቸው

ይ ገርማል ይደንቃል ደግሞም ያሳዝናል

ጥ ሎ ማለፍ ሽፍጡን ማመን አቅቶናል

ፋ ይዳ ቢሱ ፍቅር ፋታ አሳጥቶናል።

ዘውዲቱ የማነ 2019-02-19